# የነፃነት ትግል በአጥፍቻለሁ ይቅር አይካካስም

*ከበላይ መታፈሪያ*

እየታገልን ያለነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና የአገር ልዓላዊነት ነው። አገራችን በሕወሓት ነፃ አውጭ ተወራ ሕዝብ የዜግነቱን መብት ተገፎ እንደባይተዋር እየታዬ ከመሰቃየቱም በላይ አገር እየተሸጠችና በኃይል በሕገ - ወጥ ሕግ እየተገዛ ነው።

የአንድ አገር ሕዝብ ሕግ ኖሮትና ሕግን አክብሮ መኖር ደህንነትና ሰላማዊነት ነው። ነገር ግን ሕገ - ወጥ ሕግን ተቀብሎ መኖር ነፃነት የጐዳውና ያነሰው በመሆኑ ሕዝብ ይህን ዓይነት ሕግ ተቀብሎ መኖር አይቻልም። መታገልና የነፃነት መብትን ማስከበር የተፈጥሮ የመኖር ባህሪና ግዴታ ነው።

ወያኔ/ኢህአዲግ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ከፍተኛ ንቀትና ድፍረት የተሞላበት ውሸትን ዋና መሳሪያ አድርጐ ግፍ፣ ጭቆናና ብዝበዛ በመፈጸም አምባገነን ድርጊቱን ለማቆየት ኃይል ሽፍጥና ተንኰል አክሎበት ለ19ኝ ዓመት እንደቀጠለ ነው። ይህ ተግባሩን ይፋ በማድረግ የግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. ብሔራዊ ምርጫን ከሕዝብ ለአራተኛ ጊዜ ሰርቆና ነጥቆ በአጋሚዶነት በማጠናቀቅ ሰሞኑን አቶ መለስ ለስልጣን መጓጓት ያለውን ፍላጎት ለማርካት ነባር አባሎቹን በማስወገድ ሌላ የጠነከረ የታዛዥ ካድሬ ባህሪያት ያላቸውን አዲስ ካቢኔ በመምረጥ ሹምሽር ማካሄዱ ታውቋል። ቃለ ማህላ አደረገ ይባላል? ለምኑ !

የዚህ አንድ ወጥ አምባገነን ድርጅትና አጫፋሪ ምክር ቤት (ፓርላማን) አክሎ በኃይልና በሽፍጥ ስልጣን ላይ ቆይታን ማራዘም የአገር ሃብትን ለመበዝበዝ፣ ለመዝረፍና ለም መሬቷን ሽጦ ለመጨረስ፣ እንዲሁም ደግሞ ሕዝብን ለማንገላታት፣ ለማረዝ፣ አገርን ለማዳከም፣ አንድነትና ኅብረትን ለማናጋትና ለማሳነስ የሚሰራ የተለመደ ተንኰልና ሴራ በአገርና በሕዝብ ላይ አምባገነን ሥርዓት አልባነትን እንዲቀጥል መሆኑ በጉልህ እየታየ ነው።

ይህ ሕወሓታዊ ወራሪ አስተዳደር የዚህ የሰሞኑን ሹምሽር መሸፈኛ ልባስ ለመስጠት እንዲሁም ሕጋዊ መንግሥት መስሎ ለጀቲሚሲ ለማግኘት የፖለቲካ ውሽንፍር ለመፍጠር አመቺ ሆኖ ያገኘውና ያቀረበው ተንኰል ወ/ት ብርቱካን ሚዶክሳን ይቅርታ ጠየቀች ብሎ እንድትፈታ ማድረግ ነበር። በዚህ ዓይነት በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ኅብረተሰብም ዙሪያ መነጋገሪያ ዜናዎችን በማወናበጃ መልኩ ለመቀየር ተሞክሯል።

# ወ/ት ብርቱካንን ስለ መልቀቅ

ወያኔ/ኢ.ህአዲግ በፈለገውና በአቀደው ወቅትና ሁኔታ፣ በመረጠው ይዘትና ሀሳብ መርጦ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስተካከል፣ አርቅቆና ጽፎ በማቅረብ ወይንም በራሷ አነሳሽነትና ፍላጎት ታድርገው ወ/ት ብርቱካን ለአቶ መለስ የይቅርታ መጠየቂያ ደብዳቤ አቅርባለች። ለዚህም አጥፍቻለሁ ማመልከቻ ወያኔ በሚፈልገው ሁኔታ በሽማግሌ ተብዬ ጆሌ-ደላላዎች ግፊትና ጫና ተደርጐበት፣ ተመክሮም ተሰጥቷት ይሁን ተስማምታና ተቀብላ ፈርማበት ያቀረበችው የይቅርታ መጠየቂያ ደብዳቤ ተቀባይነት አግኝቶ በመንግሥት ይቅር ባይነት ተለቃለች ተብሏል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ወ/ት ብርቱካን ከአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወሮች እስራት በኋላ በጠየቀችው አጥፍቻለሁ ጥያቄ ይቅር ተብላና ይቅርታን አግኝታ መለቀቅ ለማንም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስት ዜና ነው። ከጠላት እጅ መንገላታትና ስቃይ አምልጣ ከዘመድ ፣ከወዳጅ ጋር መገናኘትዋ በእጅጉ ደስ የሚያሰኝ ነው። በመሆኑም ብዙ ኢትዮጵያዊያን ደስታቸውን፣ የሷን ቆራጥ ጠንካራ ጀግንነትና መስዋዕትነት እንደከፈለች ታላቅ መሪ እየተባለ በተለያዩ ድህረ-ገጾች ላይ በርካታ ጽሑፎችን እንዲሁም ደግሞ በሬዲዮና በፓልቶክ ተመልክተናል ሰምተናል።

ነገር ግን ወ/ት ብርቱካን ከእስር ቤት ለመውጣት፣ ለእስራት ያበቃት የራሷ ጥፋት እንደነበርና በወያኔ አስተዳደር ላይ ክህደትና ማታለል በመፈጸሟ፣ በእስራት ጊዜዋም የተጸጸተችና ብዙ የተማረችበት መሆኑን በማብራራት ለአቶ መለስ ያቀረበችው የይቅርታ ጥያቄ ጽሑፍ ደብዳቤ ይዘት በኮምፒውተር የቀረበና የደብዳቤውም ማረጋገጫ የሷ ቃል የታከለበት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተላልፏል። የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥትን በማታለሌ፣ ክህደት በመፈጸሜ አጥፍቻለሁ በስህተቴ እጸጸታለሁ **ከአሁን በኋላ በሕግ እየተመራሁና አክብሬ አርፌ አሮጊት እናቴንና ልጄን በመርዳት ጥሩ ዜጋ ሆኜ ለመኖር ነው** የሚል ቃል የሰፈረበት በደብዳቤዋና በራሷ ድምጽ ቃል ታይቷል ተሰምቷል።

ታዲያ ወያኔ/ኢ.ህአዲግ አርቅቆ ጽፎም ይስጣት፣ ጆለላዎች ተመክሮ ይታከልበት ወ/ት ብርቱካን ይህን የመሰለ የራስን የአንድን ሰው ስብዕና፣ ማንነትና ክብር በአጎደፈ ሁኔታ ዝቅ አድርጎ በማሳየት፣ ክህደትን ማታለልን ያጣቀሰ የሰውን ትንሽነት በመግለጽ አኳኋን ከእስር ቤት ለመፈታት ብቻ የወያኔን ፍላጎት ተቀብላና ተስማምታ፤ በግልጽ፣ በሀቅ የሰው ልጅ አቻነትን ስትደራደርበት ለነፃነት መታገል፣ ጨቋኝ አገር አጥፊ አስተዳደር ሕግን፣ ከራሷ አልፎ ለሌሎች መብት መቆምና መከራከር መብቷ እንደሆነ ሳትፋለም፤ እራሷን አዋርዳ የታሰረችበትን ጊዜ ጸጸት አድርጋ ኅብረተሰብን በሚያስደፍር ሁኔታ መለቀቅ እጅግ የሚያሳዝን ነው።

ወ/ት ብርቱካን ሚዶቅሳ የተማረች የሕግ ዳኛ ሕግን ተርጉማ የምትፈርድ፣ አመዛዛኝ አእምሮ ያላት፣ ያለፈውን፣ የወደፊቱ መጭውንም፣ መገምገምና ማጤን የምትችልና የፖለቲካ

ስሌቱን ሆነ ሌላውን መረዳት የሚጠበቅባት እንጂ ስብዕናን ዝቅ ማድረግ አልነበረም። እስከ አሁንም የአእምሮ ችግር ያልታየባት በእንዲህ አይነት አዋራጅ ቃላትና ተግባር አዘል ያለበት ደብዳቤ ጽፎ ይቅርታ መጠየቅ ለትግል ማነሷ ብቻ ሳይሆን እጅግ ትንሽነትንና ሽንፈትን የሚያሳይ ነው።

የዚህን የይቅርታ ጉዳይ ለመጻፍና ለመደራደር ወ/ት ብርቱካን ከራሷ ሌላ የሕግ አማካሪ ማግኘት ማማከርና መምከር ጥሩና መጥፎነቱን መረዳትና ማወቅ ተገቢ ነበር። የሕግ አማካሪ ባይፈቅድላት እንኳን በዚህ አለመደራደሩ ብልህነት ይሆን ነበር። ማንም ተራ ያልተማረ ሰው እንኳን ቢሆን ከራሱ አልፎ ዘመድ ወዳጆቹን አማክሮ ራሱንና ኅብረተሰቡንም በማያጐድፍና በማያስደፍር አኳኋን ተሸማግሎ ለመለቀቅ ይሞክራል እንጂ አገር ወገንን በሚያሳፍር አኳያ በወያኔ ፍላጎት ብቻ ራስን አዋርዶ ለመፍታት አይጥርም አይሞክርም።

አንድ ሰው እራሱን ያወቀ፣ የተረዳ፣ ለማንነቱ ባለቤት ራሱ መሆኑን ማወቅ በእኩልነት ያለ በፍጹም የማይተናነስ አቻነትን የሚያሳይ ሆኖ ማን? ምን ዓይነትና፣ ምን ማድረግ እንደሚችል? ማወቅና ማሳወቅ አለበት።

ሰው እኔነትን አውቆ ለዚያም መነሻና መድረሻ ያለው የክብር፣ ኩራት ፍጻሜዎቹን በሕይወቱ ያሳያል። ከዚህም በላይ በኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖርና የዚያን ባህላዊ ኑሮም (በኅብረተሰብ ተቀባይነት ባህሪ) አክባሪ ታዛዥና የማያዛንፍ ለተፈጻሚነቱም ከፍተኛ ኃላፊነት ግዴታ ሊኖረው ይገባል። በዚህ አኳያ ወ/ት ብርቱካን የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ ክብርና ኩራት የኅብረተሰቡን አርቆ አስተዋይነት፣ ታሪኩንና ባህላዊ ኑሮውን የማይደፍር ሕዝብ መሆኑን አላየችም፣ አላስተዋለችም፣ አልጠበቀችም። የኅብረተሰብ አካል ሆነን የዚያን ኅብረተሰብ ማንነት ለማንጸባረቅ፣ ለማስጠበቅ የእያንዳንዳችን የዜግነት ግዴታ ነው። ኢትዮጵያዊ ስሆን ኅብረተሰቡን መስዬ ስገኝ እንጂ በእኔነቴ በስሜ ብቻ አይደለም።

በፖለቲካ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ወያኔ ወ/ት ብርቱካንን ሲያስራትም ሆነ ሲፈታት ለራሱ ፖለቲካ ሂደት አስቦ የተጠቀመበት ነው። ቅንጅት እንዲፈርስ ካስደረገ በኋላ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም ዋና መሳሪያ አድርጎ የወሰደው ከማለያየት ባሻገር በማይጎዳውና በወያኔ መሰል የተደራጁትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በውሸት በማጋነንና ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ተከታይ እንዲያገኙ ሲሆን ሌላውን ጠንካራና በመርሆ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ በቆራጥነት የቆመውን ደግሞ ደካማ አድርጎ በማሳየት ተከታይና ደጋፊውን ማሳነስ የመሳሰሉት በሕዝብ ማሰራጫ ሚዲያ እንዲፈጠሩ በማድረግ ጥረት ሲደረግበት ነበር።

በዚህ ሁኔታም ወ/ት ብርቱካንን ተጠቅሞ ለማሰርና አሁን ደግሞ በአዲስ መልክ ካቢኔ ሲመርጥና መንግሥት ነኝ ሲል እውቅና ለማግኘት፣ ጥሩ ፍትሃዊ መንግሥት መስሎ በዓለም ኅብረተሰብ ለመታየትና ለመታወቅ የተጠቀመበት የፖለቲካ ውሸንፍር ነው።

ወያኔ/ኢ.ህአዲግ ከሕዝብ የ2002 ግንቦት ምርጫን በኃይል ነጥቆ በሚሿሿምበት ወቅት እንደ ሕጋዊ መንግሥት በማየትና በመገመት መንግሥት ብሎ ይቅርታ መጠየቅ፣ የፖለቲካ እውቅና ፕሮፓጋንዳ መንዣ መሆንን አለመገንዘብና አለመረዳት፣ ለአንድ የፖለቲካ መሪ ለሚባል ሰው ለቆመለት የተቃዋሚ ፖለቲካ አለመጽናትንና ድክመትን ያስገነዝባል። ወ/ት ብርቱካን ወያኔን ያታለለች፣ የካደች ለመሆኗ ይቅርታ ጠየቀች እንጅ ወያኔን የሚፈታተን ሕጋዊ ማስገዳጃ ጥያቄዎችንም ሆነ ሌላ መደራደሪያ አቅርባ ለነፃነት፣ ለዜግነት መብት ማስከበሪያ ሳይታከልበት፣ እንዲሁም የሕዝብ ትግልን የሚያበረታታ፣ የሚያጠናክር አስተባባሪነት ያለው መልዕክት እንዲተላለፍ አላደረገችም። አጋጣሚውን ተጠቅማ ጥቂት (5-10) የፖለቲካ እስረኞች እንኳን አብረዋት እንዲፈቱ ጥረት አላሳየችም። በተቃራኒው የራሷን ስብዕና ማንነት አዋርዳና ዝቅ አድርጋ የኅብረተሰብን ባህላዊ ክብርና ኩራት ባጎደለና ባዋረደ ሁኔታ ከእስር ቤት ለመውጣት የወያኔን ፍላጎት ብቻ በሟሟላት ሽንፈት እንጅ በጀግንነት የተሰራ መስዋዕትነት አይደለም። እራስን በማዋረድ የተስማማችበት ሰነድ የኢትዮጵያን የነፃነት ትግል ታቃርኖ ያለው፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ትግል የሚዳክምና የሚጎዳ ሲሆን ለወያኔ ሕጋዊ መንግሥትነትን የሚያረጋግጥ ትልቅ የፖለቲካ ሽንፈትና ውድቀትን ያሳዬ ነው። ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ዳር ድንበርና ነፃነት ትግል ከእስራት በላይ ትልቅ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው። ይህን አርቆ ማየትና መረዳት ያሻል። ስንቆነጠጥ የምትተወው፣ የተወሰነ ጊዜ ታስረን፣ በበቃኝ በአጥፋቻለሁ ይቅርታ የምንፈታበት የነፃነት ትግል ሳይሆን የክህደትና የጥቅም፣ የራስ ወዳድነትና በዓላማ አለመጽናትን ነው።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ወ/ት ብርቱካን በደብዳቤም ላይ አክላ ያካተተችውና በቃልም እንደተናገረችው "ሕግን አክብሬ ጥሩ ዜጋ በመሆን አርፌ አሮጊት እናቴንና ልጄን በመርዳት እኖራለሁ" የሚል ቃል አለ። በዚህ አባባል ለዜጎች የተላለፈው የፖለቲካ መልዕክት እንደ እኔ ሕገ - ወጥ ሕግን አክብራችሁ፣ እኔ ያደረኩትን መንገድ መከተል አለባችሁ ማስፈራሪያና መቀጣጫ ዓይነት መሰል ይታይበታል። ትግሉ ምን ሆነና !!

ታዲያ ወ/ት ብርቱካን ይህን መሰል መልዕክት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የሚያስችል አስተዋይነት እንኳ ነው? ወይንስ ምን? ለዚህ መልስ ወ/ት ብርቱካንን የኢትዮጵያ "ማንደላ" ነች "የማትበገር አንበሳ" እንዲሁም "አንግ - ሳን- ሱ-ኪ" ብለው የሚጠሯት ይመልሱት።

ወ/ት ብርቱካን የአገር፣ የወገን ጉዳይን፣ ነፃነትን አስመልክቶ የሕዝብ ጥያቄን አንስታ ወያኔ/ኢ.ህአዲግን የተሟገተችው፣ የሕዝብ የዜግነት መብት ይጠበቅ ብላ የተፈታተነችውና

የታሰረችበት ይህ ከሆነ ታላቅም ባይሆን መስዋዕትነት ከፈለች ማለት ይቻል ነበር። ነገር ግን ይህ አልተደረገም። አሁንም ለመፈታት መደራደሪያ ሆኖ አልቀረበም። ለምን መታሰርና አሁንስ ለምን ልትፈታ ቻለች? በወ/ት ብርቱካን ታሪካዊ ትምህርት፣ ለነፃነት ተጋድሎ፣ በእውነተኛ መልካም ተግባር ትውልድን የሚያንጽ መስዋዕትነት የተከፈለው  ምንድነው? በዓለም ታላላቅ ሰማዕታት መስዋዕትነትን ከከፈሉ ጋር አወዳድራችሁና አነጻጽራችሁ እያሞገሳችሁ እንደታሰረችና አሁን ደግሞ ለፈጸመችው የይቅርታ መለቀቂያ ስህተቷ ማካካሻ የምትናገሩና የምትጽፉን ታዝቤአለሁ ታሪክ ይፈርደናል ለእውነት እንታወር። የትኛውን መርሆ አዘል ጥያቄ አንስታ በመቀስቀስና በማስተማር የወያኔን ፀረ-ኢትዮጵያዊና አንድነቷ፣ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቱን፣ ፀረ-ኅብረተሰብ አድራጎቱን፣ ጭቆናውን ተቃውማና አጋልጣ ቅስቀሳ አደረገች? ይህን ወይንም ተመሳሳይ ተቃውሞነት ያለው ጥያቄ አንስታ ለመታሰር አልበቃች ለምን ለማን ታስራ እንደነበር እሷና ባልደረቦችዋ ያውቁታል።

ከአገራችን ቀደምት አባት፣ እናት፣ ጀግና አርበኞቻችን ልቆና ጠፍቶ ባህር ማዶ በመሻገር ተወዳዳሪ ወይንም ተነፃፃሪ የተፈለገለት “ሳይገሉ ጐፈሬ” እንዲሉ እንጂ ታላቅነቱ ወይም መስዋዕትነቱ አይታይም።

እንደ እውነቱ ከሆነ ወደ ኋላ መለስ ብለን የቅንጅት ጊዜ ብንዳስስ በ1997 ብሔራዊ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለሕዝባዊ መንግሥት ለፍትህና ለሕግ የበላይነት ያበቃናል ብሎ ከፍተኛ አመኔታ የጣለበትንና አቅፎና ደግፎ ተስፋ ያሳደረበትን የቅንጅት ድርጅትን እንዲሁም ደግሞ የብዙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ደም የፈሰሰበትን፣ የእስራት፣ የስደትና የእርዛት መስዋዕትነት የተከፈለበትን እንዲበታተንና ትግል አቅጣጫውን እንዲያጣ ካደረጉት ውስጥ አንዷና ዋናዋ ወ/ት ብርቱካን ነች። ከዚህም አልፎ የፈጠረችውና መሪ የሆነችበት ድርጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በማይፈልገውና በማይቀበለው የአንድነቱ ጠንቅ በዘር በቋንቋ ላይ የተመሰረቱት ድርጅቶችን ያቀፈና ትብብር የፈጠረ ሲሆን እጃቸው በንፁሃን ደም ከተለወሰ፣ አገር አስገንጣይና አፍራሽ ጋር መመሳጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚፈልገው ትግል እንከን ነው። ይህ ደግሞ የወያኔን ፍላጐት ማሳካት፣ የአንድነታችንን፣ የነፃነት ትግልን ማዳከም ነው። በሸፍጥ፣ በተንኮል፣ በተልካሻነት ውሸት ብዙ መቆየትና መኖር አይቻልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሸት አንገሽግሾታል፣ መሮታል፣ እያቅለሸለሸው በቃኝ እያለ ነው። ይህን በቶሎ ብንረዳው መልካም ነው።

ለእውነት አንታወር። ሰው ለልጁ ውሸትን አያስተምርም፣ አይሰብክም። መስዋዕትነት ከፈለች ተብሎ በባዶ ቦታ ከአለም አቀፍ ጀግና መፈለግና ማወዳደር ራሱን የቻለ ትልቅ ስህተት ነው። አዎ በእውነት የራሱን ታሪክ ለማያውቅና በራሱ ለማይኮራ እራሱን መሆን ያልቻለ እንደ ወያኔ፣ የውጭ ባለታሪኮችን ቢተርክ ቢያወራ አይገርመኝም። የወያኔ ፍላጎት ነውና። ለድክመት

ማካካሻ ምክንያቶችን መስጠት፣ ያልሆነውን፣ ያልተከፈለውን መስዋዕትነት እንደተከፈለ አድርጎ ሰማዕታት እያሉ መጥራት በእውነት ለህሊና የሚቀፍ በሽታና ለታሪክም ጥቁር ነጥብ ነው።

የአገራችንን ታሪክና ባለታሪኮችን አንስቶ አለማውራትና አለማስተማር፣ የሰማዕታት መስዋዕትነታቸውን እንደ አርአያ አለመጥቀስ እጅግ ትልቅ ስህተትና አለማወቅ ከዚህ አልፎም ለትግል በቁርጠኝነት አለመቆምን ያሳያል። ይህ ደግሞ ከአለንበት የነፃነት፣ የአገር ዳር ድንበር ትግል ተቆርቋሪነት እንዲሁም ለትውልድ ኃላፊነትና ግዴታን አለማወቅና ያላማሳወቅ፣ ታግሎ መታገልን ያራቀ ያሸሸ ነው።

በዚህ አኳኋን ኢትዮጵያን አላወቅንም ታሪክን በተገቢው አልተገነዘብንም እንዲሁም ደግሞ ለራስ ነፃነትና መብት ብቁ አልሆንም ማለት ነው።

# ኢትዮጵያን እንወቅ

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ታላቅ የሰባት ሺህ ዓመታት በላይ መንግሥትነት ያላት አገር ናት። በዓለም ከቻይና ቀጥላ በሁለተኛነት መንግሥት የመሰረተች አገር ኢትዮጵያ ናት።

በነፃነት የኖረችና ለነፃነት ትግል ከራሷ አልፎ ለዓለም ኅብረተሰብ በተለይ ደግሞ ለጥቁሩ ዓለም አርአያነት፣ ከዚያም በላይ ከሌሎች አገሮች ጎን በመሰለፍ ታላቅ የነፃነት ተጋድሎ አስተዋፅኦ የከፈለችና ያበረከተች ወደር የሌላት አገር ናት። የአውሮፓን የኰሎኒያል ወረራ ፖሊሲ ያስቀየረች በአንድነቷና በኅብረቷ ዓለምን ያስደነቀች መሪ ምሳሌነት ያላት አገር ኢትዮጵያ ናት። በዚህ የላቀ ታሪክ ይህ ትውልድ ሊኮራና ሊደፋፈርበት የሚገባ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ አለው።

የእኛ ቀደምት ትውልድ ለዘመናት አገርን ለመጠበቅ፣ ሉአላዊነትንና የሕዝብን ደህንነት ለማስከበር ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው በደምና በአጥንት የተገነባች አገር ኢትዮጵያን አቆይተውልናል። ለዚህ አያሌ ባለታሪክ መስዋዕትነትን የከፈሉ ሰማዕታት፣ ቅዱሳን አባቶችና እናቶች አሉን። ከቅርብ ጊዜያት እንኳን ብንጀምር ዓፄ ቴዎድሮስ፣ ዓፄ ዮሐንስ፣ ዓፄ ምኒልክ አቡነ ጴጥሮስ ብዙ ብዙ አሉን። ራስንና የራስ የሆነውን በቅድሚያ ማወቅ መልካም ነው። ለወጣት ትውልድ ቢነግሩት ታሪካዊ ትምህርት፣ ኩራት፣ ፍቅራዊ ዋስትና አለኝታ ሃብት ነው። ለመስዋዕትነት ባህር ማዶ ተሻግሮ ሌላ ባለ ታሪክ ምሳሌ መውሰድና መጥቀስ ትግል ካለመሆኑ በላይ የራስን ታሪክ መዘንጋትና መቅበር ይሆናል። ያም ደግም የጠላት ተግባር ነው።

ነፃነት ዋጋ አለው። ያልተከፈለበት ነፃነት የለም። ዋጋውም ደም ነው። መታሰርና መፈታት ብቻ በቂ አይደለም። ነፃነት የደም ዋጋ ትልቅ ክፍያን የሚጠይቅና፣ የጠየቀ ያለና የሚኖርም ነው። ኢትዮጵያ ለዘመናት የቆየለን የኛ ቀደምት ትውልድ ደማቸውን ከፍለው ነው። በዚያ መስዋዕትነት

ደም ኃይልና መሳሪያ ሆኖ ሕዝብን በቆራጥነት አስተባብሮና አጽንቶ ለድልና ለነፃነት በማብቃቱ ለዚህ ዛሬ ለአለነው ኢትዮጵያዊ ትውልድ አድርሷል።

በዚህ ታላቅ የጀግና አርበኞች የመልካም ታሪክ ምሳሌነት ሕያው መሰረታዊ አኗኗርና የነፃነት ዋና አብይ ጉዳይ ለትውልድ ኩራትና ሃብት ሆኖ ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር አድርጓል። እኛም ከዚያ ትውልድ የመጣን ስለሆነ ያን ባህሪ፣ ወግና ሃብት የወረስን ያን ክብር ጠብቀን፣ እራሳችንን አስከብረን ለመጪው ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን ማውረስና ማስተላለፍ፣ ኃላፊነት፣ ግዴታም ይሆንብናል። ከዚህ ያነሰ መስዋዕትነትም ሆነ ኢትዮጵያዊነት አይሆንም። ኢትዮጵያን በዚህ ታላቅ ታሪኳ የሚያውቅና የሚያሳውቅ እንጂ ይህ የጎደለው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ሊወክልና ሊናገር ለመምራት ከቶውንም አይቻልም።

የአገር አንድነት፣ ሕዝብ የመንግሥት አምንጭነትና የሕግ የበላይነት እንዲገኝና እንዲኖር ማድረግ የአንድ አገር ሕዝብ የጋራ ትግል ነው። ነፃነት የእያንዳንዳችን እንዲሁም በአጠቃላይ የአገርና የሕዝብ መብት ነው። አገራችን ኢትዮጵያ ያጋጠማትን የነፃነት ችግር ለማስወገድ የሕዝብን ትብብርና ያላሰለሰ ጥረት ያሻል። ለነፃነታችን በቆራጥነት ያለማወላወል በፅናት ስንታገልና ታግሎም ለማሸነፍ ዓላማና ግብን መነሻ አድርገን ነው። ድል የሚገኘው ግብን ዓላማ አድርጎ በተነሳ ሕዝብ በሃቅና በቆራጥነት ሲታገልና በትግል ሜዳ ተፈትኖ በተገኘ ጀግና በሕዝብን ወገን ሲመራ ነው። ሕዝብ ለዚህ የነፃነት ትግል ትልቅ ኃላፊነትና ግዴታም ስለአለው በቀደምት ትግሉን የሚመራ ባለቤት መሆን አለበት። ስለሆነም ከመቸውም በላይ ይህ ወቅት ጽናትን የሚጠይቅ ጥበብ ብልሃትን፣ አስተዋይነትንና ትዕግሥትን አስተባብሮ የቀደምት ትውልድ ስልትን በመከተል ለነፃነታችን፣ ለአንድነታችን፣ ለአገር ልዓላዊነት አስተዋጽኦ ይኑረን፣ ያለንበትን ሁኔታ ተረድተንና አገናዝበን፣ አመለካከታችንን አስተካክለን እውነትን ዋና መሳሪያ አድርገን ለመጪው ትውልድ ለልጆቻችን ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ እንደነበረችው ለማቆየትና ለማውረስ እንቁም ! እንታገል! ለድል በቶሎ የሕዝቧን ነፃነት እናስገኝ።

**ለእውነት እንታወር** !!!

**ምንጊዜም ኢትዮጵያ** !!!